# መግቢያ

ቅዳሴ ቃሉ የግእዝ ነው። የግእዝ ቤተ ሰብ በሆኑት በሌሎቹም የሴም ቋንቋዎች ሁሉ በዕብራይስጡም፣ በሱርስቱም፣ በዐረቢውም ቃሉ ተመሳሳይ ነው። ወደ አማርኛችን ሲመለስ፣ ባጭሩ ምስጋና ማለት ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት፣ ቅዳሴ ሲባል ከቅዱስ ቍርባን ጋር የሚፈጸም ዐቢይ ጸሎት ነው። ስባሔና ውዳሴ የተባሉት የግእዝ ቃላትም ጸሎተ ቅዳሴ በሚለው ክፍል ይታቀፋሉ።

ጸሎተ ቅዳሴ ለሌሊቱና ለመዓልቱ ሰዓታት ፣ለማኅሌቱና ለሰብሐተ ነግሁ (ለጥዋትና ለሠርክ ጸሎት) ማሳረጊያና ማጠቃለያ ነው።

ቅዳሴ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ቅዳሴ እየተባለ ይጠራል። ማናቸውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ የሆነ ሁሉ፣ በቅዳሴ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን እየተገኘ፣ ጸሎተ ቅዳሴውን በመሳተፍ ቅዱስ ቍርባን እንዲቀበል፣ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ታዝዞአል።

ስለዚህም ከካህናት ጀምሮ እስከ ተራው ምእመን ድረስ ያለው ሁሉ፣ በቅዳሴ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን እየተገኘ የሚነበበውን መጽሐፍ፣ የሚዘመረውን መዝሙር፣ የሚጸለየውንም ጸሎተ ቅዳሴ በእዝነ ልቡና በብረከ ኅሊና ሆኖ መስማት፣ ተሰጥዎውንም መቀበል ይገባዋል። ጸሎተ ቅዳሴውም እስኪፈጸም ድረስ መታገሥና መጸለይም አለበት። በመጨረሻም ድኅነተ ነፍስ የሚሰጠውን የጌታችንን ሥጋና ደም መቀበል ይገባዋል። ይህን የማይፈጽም ከሆነ ግን፣ ከማኅበረ ክርስቲያን መለየት እንዳለበት ቀኖናው ያዝዛል። ይህንንም ለመረዳት በጸሎተ ቅዳሴው መግቢያ፣ በዜማ፣ «ሃሌ ሉያ፣ እመቦ ብእሲ እምእመናን...» የተሰኘውን ቀኖና ጠንቅቆ ማወቅ፣ ልብ ብሎም ማስተዋል ተገቢ ነው።

ጸሎተ ቅዳሴ በሦስት ታላላቅ ምድብ ይከፈላል:-

ክፍል ፩. ከቤተ ልሔም አንሥቶ፣ ካህኑ በቤተ መቅደሱ ተገኝቶ፣ «ሚመጠን ግርምት ዛቲ ዕለት…» እያለ እስከሚያ ቀርበው ጸሎት ድረስ ያለው ክፍል ነው።

በዚህም ክፍል መሥዋዕት የምንለው ቍርባን (ኅብስቱና ወይኑ) ቤተ ልሔም ወይም ምሥጢር ቤት በምትባለው ከቤተ መቅደሱ በስተምሥራቅ ባለችው፣ ራሱን በቻለ አጥር በተከበበችው ቤት ውስጥ፣ በቀኖና የታዘዘው ጸሎት እየተጸለየ ይዘጋጃል።

በቤተ ክርስቲያኑም ውስጥ፣ የዕለቱ ቀዳስያን (ልኡካን) የሚለብሱአቸው አልባሳተ ክህነት (የመቀደሻ ልብሶች) በሊቀ ጳጳሱ፣ ሊቀ ጳጳሱ ከሌለም በዐቢይ ካህን (በሊቀ ደብሩ) ይባረካሉ። ከዚያም ልኡካኑ በቁመት፣ በሰውነት ልክ የሚመጥናቸውን እያዩ ይለብሳሉ።

ዋናው ካህን (ሠራዒው) ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ፣ የታዘዘውን ጸሎትና ስግደት ያደርሳል። ከዚያም ወደ መንጦላዕቱ (ወደ መጋረጃው) ውስጥ ለመግባትና መጋረጃውን ለመግለጥ የሚያስችለውን ጸሎት ይጸልያል። በመቀጠልም ንዋያተ ቅድሳቱን ማለት (ጻሕሉን ጽዋውን፣ ዕረፈ መስቀሉን፣ ማንካውን፣ መሶበ ወርቁን) በሊቀ ጳጳሱ፣ ሊቀ ጳጳሱ ከሌለም በዐቢይ ካህን ያስባርካል። ሁለቱም ከሌሉ ራሱ ይባርካል።

በጻሕሉ፣ በጽዋው፣ በዕርፈ መስቀሉ ላይ፣ በመሶበ ወርቁ ላይና በማኅፈዳቱ (በአልባሳቱ) ላይ የሚጸለየው ጸሎት እንዳ በቃም፣ ጻሕሉን፣ ጽዋውን በማኅፈዳቱ ያከብራል (ያለብሳል)። በዚህ ክፍል እንዲጸለይ የታዘዘውን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ፣ ዲያቆናቱና ንፍቀ ካህኑ (ረዳቱ) ቍርባኑን በመሶበ

ወርቁና በጽዋ አድርገው፣ በታላቅ ክብርና በማዕጠንት ከቤተ ልሔም ወደ ቤተ መቅደሱ ይዘው ይገባሉ።

ክፍል ፪. ካህኑ፣ «ሚመጠን ግርምት ዛቲ ዕለት...» በሚ ለው ሁለተኛው የጸሎተ ቅዳሴ ክፍል ይጀመራል፤ ሌሎቹንም ጸሎቶች ያደርሳል። በዚህ ጊዜም ካህናቱና ምእመናኑ በቀኖናው የታዘዘውን ጸሎት በዜማ ያደርሳሉ።

ይህ ክፍል ዐበይት የሆኑትን (ዋና ዋናዎቹን) ጸሎቶችና ዜማዎችን ያካተተ ነው፤ በዚህም ክፍል በቅደም ተከተል:-

አሐዱ አብ ቅዱስ
ነአኵቶ ለገበሬ ሠናያት
ንስግድ
ፍትሐት ዘወልድ (የንስሐ ጸሎት)
በእንተ ቅድሳት (የምልጃ ጸሎት) ይደርሳል።
የሐዋርያት መልእክታት ይነበባሉ፤
ቅዱስ ወንጌል ይነበባል፤
ትምህርተ ወንጌል ይሰጣል።
ከዚህም ተያይዞ፣
ጸሎተ አስተብቍዖት የምልጃ ጸሎት:-
ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት
ስለ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ዕቅበት (ጥበቃ)
ስለ ማኅበረ ክርስቲያን አንድነት ይጸለያል።

በዚህ ክፍል የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሠረተ እምነት የሆነው «ጸሎተ ሃይማኖት» የተሰኘው አንቀጸ ሃይማኖት በን ባብ ወይም በዜማ በኅብረት ይጸለያል። በመጨረሻም እግዚ አብሔር ፍጹም ሰላምንና ፍቅርን ይሰጥ ዘንድ፣ ስለ እውነተኛ ሰላምና ፍቅር ይጸለያል። በዚህ ካህኑ ምእመናን በንስሐ እየታ ደሱ (እየታጠቡ)፣ ሥጋውንና ደሙን እንዲቀበሉ ይመክራል፤ የኅጽበተ እድ (እጅን የመታጠብ) ሥርዓትም ይፈጸማል።

በጸሎተ እማኄ ጊዜ፣ ኤጴስ ቆጶሳት ከኤጲስ ቆጶሳት ጋር፣ ካህናት ከካህናት፣ ዲያቆናት ከዲያቆናት፣ ወንዶች ከወንዶች፣ ሴቶች ከሴቶች ጋር በክርስቲያናዊ ፍቅር እጅ ይነሣሣሉ። የሚለመድ ቢሆን፣ ደግሞም መለመዱ ተገቢ ነውና፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ቅድስት ኤልሳቤጥ እንዳደረጉት ትከሻ ለትከሻ መሳሳሙ የበለጠ ይሆናል፤ ምክንያቱም ሐዋርያው፣ «በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ ይላልና (፩ኛ ተሰ.፭፥፳፮)።

እስካሁን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ እንደሚታየው ግን፣ የሚቀድሱት ቀሳውስትና ዲያቆናት በአራቱ መአዝነ ዓለም እየተዘዋወሩ እጅ ሲነሡ ይታያል። ነገር ግን ይህ ሥርዓት ከቀኖና የሌለ፣ እንዲሁ በዘልማድ ብቻ የሚሠራ ነውና መቅረት ስላለበት፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል የሚል እምነት አለን።

ክፍል ፫. ይኸኛው፣ ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው ክፍሎች ይልቃል፤ ከዚህ የተነሣም ፍሬ ቅዳሴ እየተባለ ይጠራል፤ አኰቴተ ቍርባን በተሰኘው ጸሎት ይጀመራል፤ እትው በሚባለው የማሰናበቻ ቃል ይፈጸማል። ቃሉ የግእዝ ሲሆን፣ ትርጕሙም ምስጋና ማለት ነው። በዚህም መሠረት ቅዳሴአችን አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ቅዱሳን ሐዋርያት ብሎ ይጀምራል። የአባቶቻችን የቅዱሳን የሐዋርያት የቍርባን ምስጋና ማለት ነው።

በዚህ ዐቢይ የምስጋና ጸሎት፣ በጻሕል የተቀመጠው ኅብስት፣ በጽዋም የተቀዳው ንጹሕ ወይን፣ አኰቴተ ቍርባን ተብሎ በተጀመረው የምስጋና ጸሎት ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፣ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ወደ መሆን የሚለወጥበት፣ ካህናቱ፣ ምእመናኑ ቅዱስ ሥጋውን፣ ክቡር ደሙን የሚቀበሉበት ጊዜ በመሆኑ፣ በእርግጥ ታላቅ ክፍል ነው፤ ፍሬ ቅዳሴ እየተባለ የሚጠራውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን በተለያዩ ወቅቶች፣ በተለያዩ በዓላት፣ በተለያዩም አጽዋማት መድባ የምትቀድስባቸው ዐሥራ ስድ ስት የአኰቴተ ቍርባን ቅዳሴያት እንዳሉን የቤተ ክርስቲያ ናችን የታሪክ መዛግብት ያረጋግጣሉ። እነዚህም:-

፩. ቅዳሴ ሐዋርያት (አኰቴተ ቍርባን ዘሐዋርያት)
፪. ቅዳሴ እግዚእ (አኰቴተ ቍርባን ዘእግዚእ)
፫. ቅዳሴ ዮሐንስ (አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ)
፬. ቅዳሴ ማርያም (አኰቴተ ቍርባን፣ ጐስዓ ልብየ)
፭. ቅዳሴ ዘሠለስቱ ምእት ዐሠርቱ ወስምንቱ አበው
፮. ቅዳሴ ዘቅዱስ አትናቴዎስ (በ፲ኛው ምእት ዓመት የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበረ)
፯. ቅዳሴ ዘቅዱስ ባስልዮስ
፰. ቅዳሴ ዘቅዱስ ጎርጎርዮስ (የሆሣዕና ቅዳሴ)
፱. ቅዳሴ ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ
፲. ቅዳሴ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ (በመድኃኔ ዓለም በዓል የሚቀደስ)
፲፩. ቅዳሴ ዘቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ
፲፪. ቅዳሴ ዘቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ (በበዓለ መላእክት የሚቀደስ)
፲፫. ቅዳሴ ዘቅዱስ ዲዮስቆሮስ (በዘመነ ልደትና በዘመነ ትንሣኤ የሚቀደስ)
፲፬. ቅዳሴ ዘጎርጎርዮስ ካልእ (በበዓለ ልደት የሚቀደስ)
፲፭. ቅዳሴ ዘቅዱስ ያዕቆብ ሐዋርያ (የጌታ ወንድም የሚባለው፣ ነገር ግን ባሁኑ የማይቀደስ)
፲፮. ቅዳሴ ዘቅዱስ ማርቆስ (የወንጌላዊው የቅ.ማርቆስ፤ ይህም ባሁኑ ጊዜ አይቀደስም)

እነዚህን እኛ በግእዙ አኰቴተ ቍርባን የምንላቸው ቅዳሴያት፣ በፅርኡ (በግሪክኛው) የቃል ብሂል አናፎራስ (Anaphoras) እየተባሉ ይጠራሉ፤ የቍርባን ጸሎታት (ጸሎቶች) ማለት ነው።

በጸሎተ ቅዳሴያት ብዛት፣ ቤተ ክርስቲያናችን ከሕንድ ማላቫር ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀጥላ የክብር ቦታ ይዛለች። የሕንድ ማላቫር ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከስድሳ በላይ የጸሎተ ቍርባን ቅዳሴዎች ባለቤት ስትሆን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን በቀኖና የታወቁ ዐሥራ ስድስት ጸሎተ ቅዳሴያት አሉአት። የቅዱስ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መሆንዋ የሚነገርላት መዓዛ ቅዳሴ የተሰኘች ሌላ ጸሎተ ቅዳሴም አለች፤ ነገር ግን በጥንቱ የጸሎታተ ቅዳሴ መዝገብ አትታወቅም። ሆኖም በሥነ ሥርዓት ተዘጋጅተው የሚገኙ፣ በጥንታውያኑ ቅዱሳን አባቶች ስም የሚጠሩት፣ እነዚህ ሦስቱ የአኰቴተ ቍርባን ጸሎተ ቅዳሴያት (ቅዳሴዎች)፣ እንደ ሌሎቹ ቅዳሴዎች ሁሉ፣ በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ቅዱስ ሲኖዶስ ተነጋግሮ ውሳኔ ቢሰጥበት መልካም ነው እንላለን።

እንደሚታወቀው፣ ጸሎተ ቅዳሴ ካህናቱ ብቻ፤ ዲያቆናቱ ብቻ በንባብ በዜማ የሚቀባበሉት፣ ምእመናንን የሚያገልል ጸሎትና ምስጋና አይደለም። ከጸሎቱ ከምስጋናው ግማሽ በግማሽ ያህሉ የምእመናን ድርሻ ነው ማለት ይቻላል። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ የቅዳሴው ሥርዓት ገና ጥንቱን ሲዘጋጅ:-

- ይበል ካህን (ይ.ካ.)
- ይበል ንፍቀ ካህን (ይ.ካ.ን.)
- ይበል ዲያቆን (ይ.ዲ.).
- ይበል ንፍቀ ዲያቆን (ይ.ዲ.ን.) በማለት ብቻ አልተወሰነም።
- ይበል ሕዝብ (ይ.ሕ.) ብሎ የምእመናንንም ድርሻ እንደዚሁ አስቀምጦታል። ይበል ሕዝብ (ይ.ሕ.) የሚለው ቃልም ጾታን፣ ዕድሜን አይደለም፤ አይገድብም። በተለምዶ አስቀዳሽ የሚባለውን ምእመን ሁሉ ያጠቃልለዋል። የምስጋና ጸሎቱም፣ የአገልግሎቱም፣ የበረከቱም ተሳታፊ ያደርገዋል።

መጽሐፉም ጎላ ጎላ ባሉ ፊደላት ተጽፎ መቅረቡ ሌላም ጥቅም አለው፤ የዕድሜን ጸጋ ካባ የተጐናጸፉ አባቶችና እናቶች ተሰጥ

ዎውን በሚቀበሉበት ጊዜ፣ ሊያጋጥም፣ የሚችለውን የማንበብ ችግር ያስወግድላቸዋል፤ ጸሎተ ቅዳሴውን በጥሞና ለመከታተል ያስችላቸዋል።

ምእመናን የሥርዓተ ቅዳሴውን ምስጋናና ጸሎት፣ የምስጢሩንም ታላቅነት በሚገባ እንዲረዱና እንዲጠቀሙበት በማሰብ፣ ይህ የመጽሐፈ ቅዳሴ ተሰጥዎ ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት በተመሳሳይ ከተዘጋጁት ሁሉ በሁለት ምክንያቶች ልዩ ሆኖ ቀርቦአል:-

፩. መጽሐፉ የሚያካትተው የሕዝብ ድርሻ የሆነውን ቃለ ተሰጥዎ ብቻ ሳይሆን፣ ቀዳስያኑ ካህናትና ዲያቆናት ከሚያነቧቸው ከሚያዜሟቸው ክፍሎች ዋና ዋናዎቹን ጨምሮ ይዞአል።

፪. ቅዳሴ ዘሐዋርያት፣ ቅዳሴ ዘእግዚእና ቅዳሴ ዘዲዮስቆሮስ ራስ ራሳቸውን ችለው ተዘጋጅተዋል፤ ወደ ኋላ ሄዶ ገጽ በማገላበጥ የሚጠፋውን ጊዜና መደናገር አስቀርቶአል።

በጸሎተ ቅዳሴው ላይ ዲያቆኑ «አውሥኡ» ሲል ተሰጥዎውን በመቀበል ሁላችንም በዜማ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ» በማለት ድምፃችንን ከፍ አድርገን የምናሰማው ቃል፣ በላይ በአርያም ልዑል እግዚአብሔር ዘወትር በፍርሃት በረዐድ ሆነው ከሚያመሰግኑት ከሱራፌል ከኪሩቤል ጋር (ኢሳ.፮፥፫፤ ራዕ.፬፥፰) በምስጋና የሚያስተባብረን፣ አንድ የሚያደርገን፣ ከመዐርገ መላእክትም የሚያደርሰን ምስጋና መሆኑን ዐውቀን፣ እኛም እንደ እነርሱ በፍርሃት በረዐድ ሆነን ጸሎተ ቅዳሴውን መከታተል፣ ተሰጥዎውንም መቀበል ይገባናል።

ይኼም ብቻ አይደለም፤ ከኃጢአት፣ ከበደል፣ ከክፋት፣ ከተንኮል ርቀን ሁሌም በንስሐ ራሳችንን አዘጋጅተን፣ ሕይወት መድኃኒት የሆነውን ሥጋሁ ወደሙን በየጊዜው እየተቀበልን፣ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታችን ጸንተን መኖር አለብን። ይህ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነውና።

ለዚሁም ስለ ኃጢአታችን ስለ በደላችን ፀዋትወ መከራን ሁሉ በፈቃዱ ተቀብሎ፤ በመልዕለተ መስቀል ተሰቅሎ፣ ካሳ (ወጀ) ከፍሎ ያዳነን፣ ይቅርታና ምሕረት፣ ቸርነት፣ ርኅራኄና በጎነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነው፣ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይርዳን። የምሕረት አማላጅ የሆነችው ቅድስት ድንግል እናቱ እመቤታችንም በጸሎትዋ በአማላጅነትዋ ትታደገን፤ አሜን።